# ግራጫ ቃጭሎች፤ መዝገቡ፣ ትውስታ እና አጋር ፍለጋ

**በBaruk B. Spinoza**

ይህ አጭር ፅሑፍ የዛሬ አምስት ስድስት ዓመት ቀርቦ ከነበረ ጥናታዊ ፅሑፍ ላይ የተቀነጨበና ለፌስ ቡክ እንዲስማማ ተደርጎ የተቀናበረ ነው፡፡ የአዳም ሥራዎች ውስጣቸው ገና ብዙ አለ፡፡

ግራጫ ቃጭሎች የመዝገቡ ያለፈ ህይወት መዝገብ ነው፡፡ የተቀናበረ መዝገብም አይደለም ካለማንም ጣልቃ ገብነት ዱብ ያለ መዝገብ እንጂ (አዳም በመግቢያው እንዳለው ውስወሳ ጣልቃ መግባትን ያመለክታልና) መዝገቡ፣ በመዝገቡ መዝጋቢነት መዝገብ የሆነው ደግሞ ከትውስታዎቹ ነው (የኔ ስራ መመዝገብ ነው ይለናል)፡፡

ግራጫ ቃጭሎችን እንዳነበባችሁት በሁለት ክፍሎች የተከፈለ ነው፣ የመዝገቡ ልጅነትና ጉርምስና በንፋስ መውጫ ክፍል አንድ፤ ከጉርምስናው እራሱን ችሎ አግብቶ ያለፈ ህይወቱን መከለስ እስከጀመረበት ዘመን ክፍል ሁለት ሆኖ፡፡ ስለዚህ ጠቅላላ ልብወለዱ ትውስታ ላይ የተመሰረተ ግለታሪካዊ ልብወለድ ነው--ልብወለድ ውስጥ ያለ ልብወለድ (ግራጫ ቃጭሎች በሚል ርዕስ ልብወለድ እየፃፈ እንደሆነ ይነግረን የለ?) ወይም እያንዳንዱን ታሪክ (122 ርዕስ ያላቸው ታሪኮች አሉ) እንደ አንድ የእንጀራ ዓይን ከወሰድነው (በዘፈቀደ ማለት ባይቻልም ያለጋጋሪዋ/ው ጣልቃ ገብነት እንደሚወጡት የእንጀራ ዓይኖች) እዚህም እዚያም በመዝገቡ አዕምሮ ውስጥ የፈሉ ያለፉ ትውስታዎች ተመዝግበው የፈጠሩት ዶሴ ነው፡፡ ምናልባት ስደራ ካለ በጊዜ ላይ የተመሰረተ ይሆናል፡፡ ዶሴ ከሩቅ ጊዜ ወደ ቅርብ ይደረደራል፣ ወይም ይመዘገባል፡፡ ስለዚህ ከልጅነት ወደ አሁን ጊዜ ተደርጓል ታሪኩ የተቀመጠበት መንገድ፡፡

ትውስታ ረቂቅ ያለፈ ዘመን አሻራ ነው፡፡ ይህ አሻራ ግን ሊዘነጋ፣ ሊለወጥ፣ ሊጋነን፣ "ሊከሳ" ወዘተ ይችላል፡፡ ይህ የሚሆነው ግን ትውስታው በራሱ ሳይሆን ትውስታውን በተሸከመችው ግለሰብ አዕምሮ ውስጥ ነው፡፡ ያንን ያለፈ ትውስታ ግለሰቧ እንደገና ስትጠራው፣ ወደ አሁን ጊዜ ስታወርደውና ለሌሎች በትረካ ስታቀብል የሚሆን ነው፡፡ እንጂማ ራሱ ያለፈውን ሁነት ማን እንዳለ አግኝቶ ሊለውጠው ይቻለዋል? ስለዚህ ትውስታ ቀለሙ ጥርት ብሎ ነጭ ወይም ጥቁር አይሆንም ከሁለቱም የተደቀለውን ግራጫ እንጂ (ግራጫ ልብወለዱ ውስጥ ብዙ ትርጉሞች እንዳሉት ሳንዘነጋ ነው ይሄ)፡፡ ይህ ግራጫ ትውስታ ደግሞ አንዱ አንዱን እየጠራ ይግተለተላል እንጂ የተጎነጎነ ሤራ አይኖረውም፡፡ የጥሪው ድምፅ ደግሞ እንደ ደወል ነው--ትዝታው ኪል........ ኪል.........ልልልል ይላል፣ እዚያ ስንሄድ ሊዳሰሱ የሚፈልጉ በትውስታው ውስጥ ያሉ ሌሎች ትውስታዎች ቦግ ቦግ፣ ኪል ኪል ይላሉ እንደ ህፅኖቹ፡፡ ለኔ ግራጫ ቃጭሎች የተባለው ለዚህ ይመስለኛል፡፡

ከላይ ትውስታ ሊረሳ ይችላል ብለናል፡፡ እንዳውም አዳም ልብወለዱ "የመርሳት ጥበብ" እንደሆነም ይነግረናል፡፡ ሁለት አስረጂዎች አሉን፡፡ ልብ ብላችሁ ከሆነ፣ ገፅ 22 ላይ መዝገቡ እዛች ጉብታው ላይ ሆኖ አንዲት ሴት እየተብከነከኑ የሚሉትንና የሚሆኑትን ይታዘባል፡፡ ሴቲቱ ደጋግመው "ከቴም" ይላሉ፣ የታሪኩ መቋጠሪያ ርዕስም ይኸው ቃል ነው፡፡ መዝገቡ ምን ይነግረናል፣ እዛች ቦታ የፀሐይ እናት ሲባሉ ያውቃቸዋል እንጂ ስማቸውን ረስቶታል ("ስማቸው አፌ ላይ አይመጣልኝም፡፡ ቀላል ነው ግን አይያዝልኝም")፡፡ ነገር ግን ገፅ 149 ላይ ስማቸውን መርሳቱን ረስቶ "ከቴም አሉ እትዬ አስካለ" ይለናል፡፡ በተመሳሳይ፣ ገፅ 143 ላይ መዝገቡን ሦስት ሰዎች ያጋጥሙታል፡፡ ስለ እንጀራ እናቱ መልካምነት ሊያወሩ ይጀምራሉ አንዱ ምን ይላል፣ "ዘነቡ መልካም አንገት አላት"፡፡ መዝገቡን ያቀሰለችው አስተያየት ነበረች፡፡ ጉዳያችን ከስሙ ነው፡፡ ዘነቡ፣ ዘነበች፡፡ ይህን ስም ሌላ ቦታ ገፅ 96 ላይ አንስቶታል፡፡

ለመጀመሪያ ጊዜ ሮዝ መስቲካ ያስቀመሰችው ልጅ ስም ነበር፡፡

"መስቲካውን በአፌ አስገባሁ፡፡ ሙቅ፣ እርጥብ የሚያዳልጥ ነበር፡፡ እንደ ሽቶ ነበር ጠረኑ፡፡ ዘነበችን የበላሁዋት መሰለኝ፡፡ ፀጉሯን፣ እግሮችዋን፣ ማተቧን፣ ቀሚሷን፣ ጫማዋን፣ ሁለመናዋን በአፌ አስገብቼ የማላምጣት መሰለኝ (ዛሬ ዘነበች የተባለ ስም ስሰማ ሮዝ ቀለም ያለው መስቲካ ይሸተኛል፤ ሮዝ ቀለም ያለው መስቲካ ሳይ ዘነቡ ትዝ ትለኛለች)"፡፡ ነገር ግን በምንም ተዓምር ይህን ከመልካም ትዝታ ጋር የተያያዘ ስም ከእንጀራ እናቱ ጋር ማዋደድ አይፈልግም፡፡ ሆን ብሎ አይደለም የsub-conscious አዕምሮው ስራ ሆኖ እንጂ፡፡ እናም የእንጀራ እናቱን እእ ይላታል ለስም ያህል፣ በቤት ውስጥ ሙያዋ፡፡

የመዝገቡ መዝገብ መፅሐፉ ሲያልቅ እንደሚመጣው የፎቶ አልበም ነው፡፡ በቃላት የተነሳ፣ የተነደፈ፣ የተሳለ የፎቶግራፎች አልበም ነው፡፡ አልበም ሤራ የለውም፡፡ የዘመን አሻራን፣ በዚህ ጊዜ እንዲህ ነበር ለማለት ያህል ይሆናል እንጂ (ለዚያውም ፎቶዎቹ መነሻ ሆነው ለተያያዥ ትረካ)፣ ፍፁም ምሉዕ የሆነ የትዝታውን መረጃ አይሰጥም፡፡ ግን ግን፣ ሤራ የለውም ማለት ታሪኮቹን የሚያይዛቸው አንድ ቀጭን ክር የለም ማለት አይደለም፡፡ ተደጋግሞ መፅሐፉ ተጀምሮ እስኪያልቅ የሚመዘዝ ቀጭን ሰበዝ አለ፣ የተለያየ ቀለም ያለው---ይኸውም አጋርን ፍለጋ ነው፡፡

መዝገቡ ገና እንቡጥ ሳለ በሦስት ዓመቱ እናቱን በሞት ያጣ ሰው ነበር፡፡ ይህ ሰው ወደዚህ ምድር ለመምጣቱ ምክንያት ከሆነው አባቱ ጀምሮ ማንም ቁብ ያልሰጠው ሰው ነበር፡፡ አንደበቱን በተካው ፅሑፍ እንዲህ ይለናል “በየቤታቸው ያሉ ሰዎችን ከኔ የሚለያቸው አንድ ትልቅ ጉዳይ ከሌሎች ሰዎች ጋር መሆናቸው ነበር፡፡ እኔ እዚያች ምልዕልቴ ላይ ብቻዬን ነበርኩ፡፡ ከቤቴ ደ'ሞ ተጨንቆ ራት እንድበላ የሚጠራኝ ማንም የለም፡፡ ሁለመናዬ እንደሌሎች ቢሆንም፡፡ የምቀርበው የማፈቅረው የማምነው ሕፃን ጓደኛ አልነበረኝም” (ገጽ 4)፡፡ እዛው ጥቂት ወረድ ብሎ ታዲያ እንዲህ ይቀጥላል “እግዜር ፍጡርን እዚህ ምድር ሲያመጣ ጀምሮ…ትልቁ ያስቸገረው ነገር ለፍጡራን አጋር የመስራት ነበር (ሄዋንን ለመፍጠር ታዲያ ለምን ዘገየ? አጋር መቀመሩ ከብዶት ይሆን?)፡፡ ለወንድ ሴት፣ ለሴት ወንድ አለው፡፡ ለልጅ አባት አለው…ያለ አጋር እግዚአብሔር ምንም ነገር አልሰራም…እሱም ነገሩ ገብቶት ነው መሰለኝ (ቢከብደውም)…ለእኔም አጋር ሰጥቶኛል….. አንድ ብቻ ሳይሆን……. [ብዙ]”ይላል፡፡ አምፖል፣ ጉብታው፣ አካባቢው፣ የወደቁ ነፍሳት፣ ማለዳ የሚጠብቃት ፀሐይ፣ ናና ከረሜላ ወዘተ፡፡ ወሰንየለሽን አጋሩ ሊያደርግ ሞክሮ ከሽፈበት፡፡ ከዚያ ኤልያስን አገኘ፡፡ ከዚያ ወለዬውን፡፡ ከሁሉ የሞላችው ግን ገነት ናት፡፡ ያለፈ ቁስሉን በመሳም የደመሰሰችለት አዲስ አድማስ የገለጠችለት፣ ጣዕም የሰጠቸው፣ “ተጣጥፋ አፉ ውስጥ እንደ ናና ከረሜላ”ው የሆነች፡፡

መዝገቡ “…….የሆነ የተጋረደ ነገር ወደቀ…….” ከማለቱ በፊት በእሱ እና በገነት መሃል፣ ወለዬው እንዲህ ብሎት ነበር፣ “እኔ አደርጋለሁ፡፡ ስህተት አላሳልፍም፡፡ ሰው አያስፈራም፡፡ ማየት ምን ይጠቅማል? ለመውደድ ለመጥላት ካልወጣህ? ትንሽ ካልረበሽክ፣ ትንሽ የአንተን ቦታ ካላሳየህ መፈጠርህን ማስመስከር አለብህ፡፡ እዚች ምድር ላይ እንደነበርክ ማሳየት አለብህ [….]” (ገጽ 341)፡፡ የመዝገቡ ዓይን ተከፍቶለታል በዚህ አባባል፣ “በራሴ የብቸኝነት ጎዳናዬ ላይ ያጋጠሙኝን ሰዎች በግዴለሽነት ከማወቅ ሌላ ሰውን ልወዳጀው፣ ተጋጭቼ ላርመው የፈለግሁበት ጊዜ አልነበረም፡፡ ጉዋደኛ የመሆን ፍላጎት እንኩዋን ቢኖረኝ በቸልተኛነት አስቀረዋለሁ፡፡ ተጣልቼ አላውቅም፡፡ አፍቅሬ አላውቅም፡፡ በአካባቢዬ የተሳሳተ ነገር ባይ ለማስተካከል ከሰው ጋር መሆን እንዳለብኝ እዘነጋለሁ [….] (ገጽ 342)፡፡ በገነት ፍቅርን ቀመሰ፡፡ ባለፈ ዘመኑ ሁሉ ሰዎች ያጡት “ትንሽ ፍቅር” እንደሆነ ተገለጠለት፡፡ ለራሱ መቆምን ሃ ብሎ ታዲያ ሲጀምር፣ በነገር የሚተነኳኩሰውን በኩረን በመምታት ነበር፡፡ እናም እንዲህ ይላል ገድሉ ሁነት ላይ ቆሞ፣ “አምፖል እያየሁ አይደለም፣ ንፉስ መውጫን እየጣልኩ ነው፡፡ በደም ስሮቼ የሚሮጠው እንደ እሳት የቀጠነ ደም ነበር፡፡ ሽፋሽፍቶቼ እንደ ሲሚንቶ ከረዋል፡፡ የበኩረን ቦግ ያለ ጨለማ ፊት በቅንድቦቼ እየቀደድኩት ነበር፡፡ ማዕከሉን እየተጋፋሁ፡፡ አውቃለሁ ለመሞት ወይም ለመኖር እየለፋሁ እንደሆነ (ገጽ 437)፡፡ “መመዝገብ ትርጉሙ ማየት፣ መስማት፣ ማሽተት ማለት ነው” (ገጽ 10)፡፡ ከነዚህ ሁሉ ደግሞ ማየቱ ይበልጣል፣ መዝገቡ ተመልካች ነበረ (ለዚህም ነው የመፅሐፉ የሽፋን ስዕል ላይ የመስገቡ ዓይን ትልቅ የሆነው፣ ቀጥሎ ደግሞ አዳማጭ ነው ስለዚህ ጋለል ብሎ በጆሮው ያስገባል)፣ እንጂ አድራጊ አልነበረም፡፡

መዝገቡ አጋሩን ሲያገኝ፣ እርስዋም የርሱ ብቻ እንደሆነች ሲሰማው ለመጀመሪያ ጊዜ አይኑ ሲገለጥ በርሷ የመጣን በመጣል አምሳል ያለፈ ህይወቱን ሁሉ ገፎ ጥሎ አዲስ ቆዳ ሲያወጣ፣ ያለፈ ህይወቱን በትንታኔ ትርጉም በመስጠት መከለስ ቻለ፡፡ ባለፈ ህይወቱ እና ዛሬ በደረሰበት መካከል ያለውን ትልቅ ገደል ማየት ቻለ፡፡ እና ያን ከገደሉ ማዶ ያለ ህይወቱን ከትውስታ ማኅደሩ እየጠራ፣ ወደ አዕምሮው ተሰልፎ ተግተልትሎ እንደመጣለት እውነቱን ልብወለድ አድርጎ ፃፈው፡፡ እኛም በአዳም ድልድይነት አነበብነው፡፡

እና ይሄ ነው የታየኝ፣ በመዝገቡ በትውስታ እና አጋርን በመፈለግ መካከል ያለው ግንኙነት፡፡ ግን እንዲህ እንደተፃፈው ብቻ ሳይሆን እጅግ ጥልቅ የሆኑ ፍተሻዎችን የሚጠይቅ ጉዳይ መሆኑን ማስታወሱን አልዘነጋም፡፡